ልዩ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ
LIYU MICROFINANCE INSTITUTION S.C

ቀን መስከረም 11, 2017 ዓ.ም.

ቁጥር ቦዳ/547/17

**የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማኅበር**
**ዳሽን ባንክ አ.ማ**
**አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ**
**የአዲስ አበባ ነጋዴ ሴቶች ማህበር**
**የኢትዮላይፍ ኤንድ ጀኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ**
**ፕሮጃይኒስት**
**አቶ ኃይሉ ወንድአፍራሽ ወልደአማኑኤል**
**አቶ ተወልደብርሃን ገ/ጻዲቅ ገ/ስላሴ**
**አቶ አየለ ቦጋለ ገዳሙ**
**አቶ መንግስቱ መሐሩ**
**አቶ ሰለሞን ወ/ጊዮርጊስ**
**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ፡-የ10ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እና 30ኛ ዓመታዊ ያልሆነ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ድ.ሪ ንግድ ህግ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 366(1)፣367(2)፣400፣398 እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ አንቀፅ 21 መሰረት የልዩ ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 10ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እና 30ኛ ዓመታዊ ያልሆነ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 9 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ 22 አካባቢ በሚገኘው ኒው ዴይ ሆቴል ይካሔዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤዎቹ ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

1. አክሲዮን ማህበሩን የተመለከቱ መረጃዎች
   1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር አዲስ የሚገኝበት አካባቢ 22 ከጎላጎል ወደ ቦሌ በሚወስደው መንገድ ኒው ዴይ ሆቴል አጠገብ ሲሆን የማህበሩ ድረገጽ አድራሻ www.liyumfi.com ነው፡፡
   1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- MFI/034/2011

1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ(ካፒታል)፦75,000,000

1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ(ካፒታል)፦75,000,000

2. **የ30ኛው ዓመታዊ ያልሆነ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**

2.1. ብሔራዊ ባንክ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት አክሲዮን ማስተላለፍ ላይ ተወያይቶ መወሰን

2.2. የማህበሩን የተከፈለ ካፒታል ማሳደግ ላይ ተወያይቶ መወሰን

3. **የ10ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**

3.1. የአክሲዮን ማህበሩን ካፒታል ማሳደግ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ

3.2. የአክሲዮን ማህበሩን መመስረቻ ፅሁፍ ማሻሻል ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ

4. **ማሳሰቢያ**

4.1. በጉባኤው ላይ መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ህግ አንቀፅ 377 መሰረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሶስት ቀን በፊት በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

4.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ።እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ(ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

የልዩ ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ።

ከሠላምታ ጋር

አባል ቦጋለ
የቦርድ ሊቀመንበር

ልዩ ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ
Liyu Microfinance Institution S.C